# የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

## የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት እና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር ፳፱፬/፪ሺ፲፫

ሐምሌ ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ በአዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ መሰረት በርካታ ስልጣን እና ተግባራት የተሰጡት ሲሆን ከእነዚህ ሥልጣን እና ተግባራት መካከል አንዱ ሪፖርት አቅራቢ አካላትን የህዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ መለየት የሚያስችል መስፈርት ማውጣት እና መመዝገብ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ቦርዱ የሪፖርት አቅራቢ አካላትን የሥራ ዓይነት ወይም ባህሪ፣ የሀብት መጠን ወይም የሠራተኛ ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት የህዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት እና አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች የሚለዩበትን መስፈርት አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ሪፖርት አቅራቢ አካላት በአዋጁ በተደነገገው የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መሰረት ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫቸውን አዘጋጅተው ለቦርዱ መቼ ማቅረብ እና ማስመዝገብ እንዳለባቸው እንዲሁም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባያቀርቡ ያለባቸውን ኃላፊነት በዚህ መመሪያ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ በአዋጁ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት የሪፖርት አቅራቢ አካላትን የህዝብ ጥቅም ያለባቸው እና አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ መለየት የሚያስችል መስፈርት ማስቀመጥ እና ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫዎቻቸውን በፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መሰረት አዘጋጅተው መቼ ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለባቸው እና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሳይወጡ ሲቀሩ የሚኖርባቸውን ተጠያቂነት ለመወሰን ነው፡፡

በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ አንቀጽ ፵፫(፪) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት እና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር ፳፻፬/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. "ቦርድ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴፪/፪ሺ፯ መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ነው፤

፪. "አዋጅ" ማለት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፯ ነው፤

፫. "ደንብ" ማለት የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴፪/፪ሺ፯ ነው፤

፬. "የሠራተኞች ብዛት" ማለት ሪፖርት አቅራቢው አካል በሂሣብ ዓመቱ በእያንዳንዱ ወር በሥራ ውል ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሆነው ወሩን ሙሉ ባይሰሩም ጠቅላላ ድምሩ በሂሣብ ዓመቱ ላሉት ወራት ቁጥር ሲካፈል የሚገኘው አማካይ የሠራተኞች ብዛት ነው፡፡

፭. "ጠቅላላ ሀብት" ማለት በሪፖርት አቅራቢው አካል የሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የሰፈረው ጠቅላላ የሀብት መጠን ነው፡፡

፮. "የሪፖርት አቅራቢ አካላት የምዝገባ የምስክር ወረቀት" ማለት ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅት መሆናቸውን የሚያሳይ በቦርዱ የሚሰጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

፯. በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፰. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል።

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋሙ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰሩ ማናቸውም ሪፖርት አቅራቢ አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት እና ምዝገባ</u>

፬. <u>ሪፖርት አቅራቢ አካላት</u>

ከዚህ በታች ባሉ አንቀጾች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ይባላሉ።

፭. <u>የህዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት</u>

፩. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሪፖርት አቅራቢ አካላት ከተሰማሩበት የሥራ ዓይነት ወይም ባህሪ አኳያ የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት ናቸው።

ሀ) የሚያወጡትን የግዴታ የምስክር ወረቀት ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለግብይት ያዋለ ወይም ለማዋል በዝግጅት ላይ ያለ ማንኛውም ኩባንያ፤

ለ) ባንኮች፣ የመድን ሰጪ ተቋማት፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያዎች እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት፤

ሐ) በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቊጥጥር ስር ያለ የልማት ድርጅት፤

መ) የአክሲዮን ማሕበር ፤

ሠ) በሚመለከተው የመንግሥት አካል ቁጥጥር የሚደረግበት የጡረታ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ የሚያስተዳድር እና ተመሳሳይ ተግባር የሚፈጽም ተቋም፤

ረ) የሕብረት ስራ ዩኒየኖች፤

ሰ) ቁጥጥር የሚደረግበት የሸማቾች ማኅበር፤

ሸ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት እና የበጎ አድራጎት ድርጅት፤

ቀ) የኢትዮጵያ የምርት ገበያ አባላት፤

፪. ከሪፖርት አቅራቢ አካል የሀብት መጠንና የሰራተኞች ብዛት አኳያ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ያሟላ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሕዝብ ጥቅም ያለበት አካል ነው፡፡

ሀ) ዓመታዊ ገቢው ብር ፫፻ ሚልዮን (ሦስት መቶ ሚሊዮን) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፤

ለ) ጠቅላላ ሀብቱ ብር ፪፻ ሚልዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፤

ሐ) ጠቅላላ ዕዳው ብር ፪፻ ሚልዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፤

መ) የሰራተኞቹ ብዛት ፪፻ (ሁለት መቶ) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፡፡

፫. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ለዚህ መመሪያ አንቀጽ ፬ አፈፃፀም ሲባል የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ ዓመት ፲፪ (አስራ ሁለት) ወራት በማይሞላበት ጊዜ በሰራባቸው ወራት ያገኘው የገቢ መጠን ሂሳብ ተሰልቶ ወደ ዓመት ይቀየራል፡፡

## ፬. <u>የአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች መለያ መስፈርት</u>

፩. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ያሟላ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል አነስተኛና መካከለኛ ድርጅት ነው፡፡

ሀ) ዓመታዊ ገቢው ብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን) እና ከብር ፫፻ ሚሊዮን (ሦስት መቶ ሚሊዮን) በታች የሆነ፤

ለ) ጠቅላላ ሀብቱ ብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን) እና ከብር ፪፻ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን) በታች የሆነ፤

ሐ) ጠቅላላ ዕዳው ብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን) እና ከብር ፪፻ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን) በታች የሆነ፤

መ) የሠራተኞቹ ብዛት ፳ (ሃያ) እና ከ፪፻ (ሁለት መቶ) በታች የሆነ፤

፪. በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፭ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ሥር የተቀመጠውን መስፈርት ባያሟላም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅት ነው፡፡

፮. <u>ጥቃቅን ድርጅቶች</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፭ እና ፮ ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የማያሟላ የሽርክና ማኅበር ወይም የግል የንግድ ድርጅት እንደ ጥቃቅን ድርጅት ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሪፖርት አቅራቢ አካላት ግዴታዎች

፯. <u>የሪፖርት አቅራቢ አካላት ግዴታዎች</u>

፩. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት የተዘጋጀ ኦዲት የተደረገ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ) የሕዝብ ጥቅም ያለበት አካል ከሆነ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች፤

ለ) አነስተኛና መካከለኛ ድርጅት ከሆነ ለአነስተኛና መካከለኛ ድርጅት በወጣው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች፤

ሐ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት እና የበጎ አድራጎት ድርጅት ከሆነ በዓለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች፡፡

፪. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሚያቀርበው ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ በዚህ አንቀፅ በተደነገገው የፋይናንስ ደረጃ እና ቦርዱ ባወጣቸው ወይም በተቀበላቸው የኦዲት ደረጃዎች መሰረት ተዘጋጅቶ በቅድሚያ ለቦርዱ መቅረብ ያለበት ሲሆን በሌሎች ህጎች ስልጣን ለተሰጠው የመንግስት መስሪያ ቤት የሚቀርበው ሪፖርትም ለቦርዱ የቀረበው ኦርጂናል ቅጂ መሆን አለበት፡፡

፫. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሪፖርት አቅራቢ አካላት ለቦርዱ የሚያቀርቡት ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ በውጪ ኦዲተር የተመረመረ መሆን አለበት፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱ ሪፖርት አቅራቢ አካላት ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫዎቻቸውን የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት በተጠናቀቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ቦርዱ በሚወስነው የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴ በመጠቀም ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ያላቀረበ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ሪፖርት አቅራቢው አካል ብር ፪፻ (ሁለት መቶ) እና የሪፖርት አቅራቢው አካል ዳይሬክተር ብር ፻ (አንድ መቶ) የገንዘብ ቅጣት ይከፍላል፡፡ ሆኖም ይህ የገንዘብ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው ለ፫ (ሶስት) ወር ብቻ ሲሆን ሦስት ወር ካለፈ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፮. በቦርዱ ያልተመዘገበ ሪፖርት አቅራቢ አካል ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወራት ውስጥ ካልተመዘገበ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ሪፖርት አቅራቢው አካል ብር ፪፻ (ሁለት መቶ) እና የሪፖርት አቅራቢው አካል ዳይሬክተር ብር ፻ (አንድ መቶ) የገንዘብ ቅጣት ይከፍላል፡፡ ሆኖም ይህ የገንዘብ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው ለ፫ (ሶስት) ወር ብቻ ሲሆን ሦስት ወር ካለፈ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፯. ይህ መመሪያ ከወጣ በኂላ የተመሰረተ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ሥራ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ ካልተመዘገበ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ሪፖርት አቅራቢው አካል ብር ፪፻ (ሁለት መቶ) እና የሪፖርት አቅራቢው አካል ዳይሬክተር ብር ፻ (አንድ መቶ) የገንዘብ ቅጣት ይከፍላል። ሆኖም ይህ የገንዘብ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው ለ፫ (ሶስት) ወር ብቻ ሲሆን ሦስት ወር ካለፈ በአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

፰. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫውን በውጪ ባለሙያ የሚያሰራ ከሆነ በቦርዱ በተመዘገበ የሒሳብ ወይም የኦዲት ባለሙያ ማሰራት እና ከሒሳብ ወይም ከኦዲት ድርጅቱ ጋር ሕጋዊ ውል መዋዋል አለበት። ይህ ካልሆነ ለቦርዱ የሚያቀርበው የሂሳብ መግለጫ እና የኦዲት ሪፖርት ተቀባይነት የለውም።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፱. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### ፲. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

እዮብ ተካልኝ (ፒ.ኤች.ዲ)

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ